# “ተነስቷል”

ፕሬዘደንት ቶማስ ኤስ ሞንሰን

ከብዙ አመቶች በፊት፣ የቴት የስዕል አዳራሽን በለንደን እንግሊዝ ውስጥ እያለሁ ጎበኘሁ። የGainsborough, Rembrandt, Constable እና የሌሎች አርቲስቶች በየክፍሉ ይገኙ ነበር። እነዚህን ስራዎች ለመፈጸም ምን ያህል ችሎታ እንደሚያስፈልግ አውቄ ወብታቸውን እደነቅበት ነበር። በሶስተኛው ክፍል ውስጥ የተደበቀው ስዕል ግን የእኔን ትኩረት እና ልቤን ነካው። ስዕሉን የሳለው Frank Bramley በሀርን የሚመለከት ትንሽ ቤትን ስሎ ነበር። በስዕሉ ውስጥም በማታም የአሳ አጥማጁ ሚስት እና እናት እርሱን ይጠብቁ የነበሩትን ያሳያል። ማታው ስለመጣ በበሀር ውስጥ እንደጠፉ ገብቷቸው ነበር።በአማቷን አቅፋ ወጣቷ ሚስት በጭንቀት ታለቅስ ነበር። በመስታዎት ያለውም ያለቀው ሻማም ለስንት ጊዜ ይጠብቁ እንደነበሩ ያሳያል።

የወጣቷን ሴት ጭንቀት ይሰማኛል፤ ሀዘኗም ተሰምቶኛል። አርቲስቱ ለስዕል የሰጠው ስምም አሳዛኝ ታሪክንም ይነግር ነበር። ይህም ተስፋ የሌለው ጠዋት የሚል ነበር።

ወጣት ሴቷ እንዲህ በሚለው በRobert Louis Stevenson’s “Requiem” ለመፅናናት እንዴት ትፈልግ ነበር፤

መርከበኛው እቤት ነው፣ ከበሀር ወደቤት ተመልሷል፣
እና አዳኝም ፣ ከተራራው ወደቤት መጥቷል።

ከምድራዊ ህይወት ሁሉ እርግጠኛ የሆነው መጨረሻው ነው። ሞት ሉሁሉም ይመጣል፤ ይህም ሁለንተናዊ ወርሳችን ነው። በህጻንነትም ወይም በወጣትነት ያጠቃል፤ ህይወት በሚጀምርበትም ሊጋብዝ ይችላል፤ ወይም የጭንቅላት ጸጉራችን ነጭ እስኪሆኑ ድረስ ይጠብቃል። በአደጋ ወይም በህመም ይድደሳል፣ ወይም በፍጥረት ጉዳይ ይመጣል፣ ግን መምጣት ይኖርበታል። ይህም ከግንኙነት መለያየትን የምጣል፣ እና በልዩ በወጣቶችም ያልተሟላን ህልም ይደመስሳል፣ ተስፋንም ያጠፋል።

የሚታየውን ከማይታየው ከሚያለያየው አጋራጅ በኋላ ምን እንዳለ የማያስብ ምን ምድራዊ ሰው አለ።

ከብዙ መቶ አመቶች በፊት ለብዙ ጊዜ በአለማዊ ስጦታዎች የተባረከው እና ሰው ሊደርስበት በሚችለው ችግሮች ሁሉ የተመታው ኢያብ ከጓደኞቹ ጋር ተቀምጦ ይህን ጠየቀ፣ “ሰው ከሞተ ተመልሶ ሕያው ይሆናልን?”3 ኢያብ በህይወት ያሉ ሰዎች የሚያሰላስሉትን ነበር የተናገረበት።

በዚህ ግርማዊ የትንሳኤ ሰንበት የኢያብ ጥያቄ “ሰው ከሞተ ተመልሶ ሕያው ይሆናልን? “ለማሰብ እና በማሰላሰል ብቻ ሳይሆን ከእግዚአብሔር በተገለጹት ቃላት የሚመጡትን መልስ ለመስጠት እፈልጋለሁ። አስፈላጊ በሆነው እጀምራለሁ።

በምንኖርበት አለም ንድፍ ካለ፣ ንድፉን የሚሰራም መኖር አለበት። የሁለንተኛን ብዙ አስደናቂ ነገሮች በመመልከት ለሰው ዘር ንድፍ እንዳለ የማያምን ይኖራል? ንድፍ የሚሰራ እንዳለስማን ይጠራጠራል?

በዘፍጥረት መፅሐፍ ውስጥ ታላቁ ነዳፊው ስማይን እና ምድርን እንደፈጠረ እንማራለን። “ምድርም ባዶ ነበረች፥ አንዳችም አልነበረባትም፤ ጨለማም በጥልቁ ላይ ነበረ።”

ነዳፊውም “ብርሃን ይሁን አለ፤ ብርሃንም ሆነ።” ጠፈርን ፈጠረ። ምድርን ከውሆች አለያየ፣ “ምድር ዘርን የሚሰጥ ሣርንና ቡቃያን በምድርም ላይ እንደ ወገኑ ዘሩ ያለበትን ፍሬን የሚያፈራ ዛፍን ታብቅል አለ።”

ሁለት ብርሀኖችንም ፈጠረ --- ጸሀይንና ጨረቃን። ኮኮቦችም በንድፉ መጡ። በውሀ ውስጥም ህያው ፍጥረቶችን እና ከምድር በላይም  የሚበሩትን ወፎች ይፈጠሩ አለ። እንዲህም ሆነ። ከብቶችን አውሬዎችን፣ እና የሚሳበቡ ነገሮችንም ሰራ። ንድፉም ለመፈጸም ቀርቦ ነበር።

ከሁሉም በመጨረሻም ህያው በሆኑ ነገሮች ላይ አለቃነት በመስጠት ሰውን --- ወንድና ሴትንም--- በእርሱ ምስል ፈጠረ።

ሰው ብቻ ነው አንጎልን አዕምሮን እና ነፍስን የተቀበለው። ሰው ብቻ ከእነዚህ መለያ ባህርይ ጋር ለእምነት፣ ለተስፋ፣ ለመነሳሳት፣ እና ለፍላጎት ችሎታ ነበረው።

የታላቁ ነዳፊ ክብራዊ ስራ የሆነው ፣ በሁሉም ህያው ነገሮች ላይ ስልጣን ያለው፣ አንጎል ፍላጎት አዕምሮ ነፍስ እና መለኮታዊነት ያለው ሰው የምድር ሰውነቱን መንፈሱ ትቶ ሲሄድ መጨረሻው ነው ብሎ በማሳመል ሊከራከር የሚችል ማን ነው።

የሞትን ትርጉም ለመገባት የህይወትን አላማ ማወቅ አለብን። እምነት ወደምድራዊ ህይወት ከመወለዳችን በፊት እንደኖርን በምናውቅበት በራዕይ በሚመጣው የእውቀት ብርሀን መብራት አለባት። ከምድራዊ ህይወት በፊት ወደዚህ ፈታኝ ቢሆንም አስፈላጊ ወደሆነው ህይወት ለመምጣት ባለን እድል ምክንያት በደስታ ከጮሁት የእግዚአብሔር ወንድ እና ሴት ልጆች መካከል እንደነበርን ጥርጥር የለንም። አላማችን ስጋዊ ሰውነት ለማግኘት፣ ፈተናዎችን ለማሸነፍ፣ እና የእግዚአብሔርን ትእዛዛት በመጠበቅ እራሳችንን ብቁ ለማድረግ እንደሆነ እናውቃለን። በምድራዊ ህይወት ምክንያት እንደምንፈተን፣ ኃጥያት እንደምንሰራ እና ፍጹም እንደማንሆን የሰማይ አባታችን አውቆ ነበር። ውጤታማ ለመሆን እድል እንዲኖረንም ለእኛ የሚሰቃይ እና የሚሞት አዳኝ ሰጠን። ለኅውጥያታችን ክፍያ ከመስጠቱ በተጨማሪ እንደ ኃጥያት ክፍያው ክፍልም በአዳም መውደቅ ምክንያት የመጣብንን የስጋዊ ሞት ያሸንፋልም።

በዚህም ከ2 ሺህ አምቶች በፊት አዳኛችን ክርስቶስ በምድራዊ ህይወት በቤትለሔም ተወለደ። ከብዙ ጊዜ ጀምሮ ይነገርበት የነበረው መሲሕ መጣ።

ስለኢየሱስ ትንሽ ልጅ ታሪክ ብዙ አልተጻፈም ነበር። በሉቃስ ላይ የተጻፈውን እውደዋለሁ፣ “ኢየሱስም ደግሞ በጥበብና በቁመት በሞገስም በእግዚአብሔርና በሰው ፊት ያድግ ነበር።”6 በሐዋሪያት ስራ ውስጥም “እርሱም መልካም እያደረገ” ሄደ የሚለውም ብዙ ትርጉም ያለው ነው።7

በዮርዳኖስ ወንዝ ውስጥም በዮሀንስ ተጠመቀ። አስራ ሑለት ሐዋሪያትንም ጠራ። የታመሙትን ባረከ። አካለ ስንኩሉ እንዲራመድ፣ አይነ ስውሩ እንዲያይ፣ ደንቆሮው እንዲሰማ አደረገ።፡ መታንንም ከሞት አስነሳ። አስተማረ፣ መሰከረ፣ እና እኛ የምንከተለውንም ፍጹም ምሳሌ ሰጠን።

ከዛም የምድራዊ ሚስዮኑ ተፈጸመ። የመጨረሻው እራት በከፍተኛው ክፍል ውስጥ ከሐዋሪያቱ ጋር በላ። ወደፊትም ገትሰመኔ እና የካልቨሪ መስቀል ነበሩ።

በገትሰመኔ ክርስቶስ ያደረገውን አስፈላጊነት ማንም ሰው በሙሉ ሊገባው አይችልም። እራሱም ይህን አጋጣሚ እንዲህ ገልጾታል፣ "ይህም ስቃይ የሁሉም ታላቅ የሆንኩትን እኔን እግዚአብሔርን፣ ከስቃዩ የተነሳ እንድንቀጠቀጥ እናም ከእያንዳንዱ ቀዳዳ እንድደማ እናም በአካል እና በመንፈስ እንድሰቃይ…አደረገኝ።"8

በገትሰመኔ ከነበረው ስቃይ በኋላ፣ ጥንካሬን አጥቶ ታስሮ ወደ ሐና፣ ቀያፍ፣ ጲላጦስ፣ እና ወደ ሄሮድስ ተወሰደ። ተከሰሰም ተሰደበም። በመገረፍም ሰውነቱ በተጨማሪ ተዳከመ። በሹክ በተሰራው ዘውድ ምክንያትም ደም በፊቱ ላይ ፈሰሰ። ከዛም "ስቀለው፣ ስቀለው" ብለው የሚጮሁትን ሰዎች ወዳዳመጠው ወደ ጲላጦስ እንደገና ተወሰደ።9

ስለት ጫፍ ያላቸው ብረት እና አጥንት የታሰረበት በጎዳ የተሰራ መግረፊያ ተገረፈ። ከመገረፉ በኋላ ተነስቶም የእራሱን መስቀል መሄድ እስከማይችል ድረስ እና ሌላ ሸከሙን እስከሚሸከምለት ድረስ እየተደናቀፈ ሄደ።

በመጨረሻም በካልቨሪ ሊረዱት የማይችሉት ሰዎች እየተመለከቱ የተቆሰለው ሰምነቱ በመስቀል ላይ ተሰቀለ። ያለምህረትም ተመትቶ እና ተሰድቦ ነበር። ነገር ግን እንዲህ ጮኸ፣ "አባት ሆይ፥ የሚያደርጉትን አያውቁምና ይቅር በላቸው።"10

በቀስታም እየሞተ እያለም በስቃይ ሰአቶች አልፉ።ከጠምው ከንፈሩም እነዚህ ቃላቶች መጡ፣ "አባት ሆይ፣ ነፍሴን በእጅህ አደራ እሰጣለሁ…ይህንም ብሎ ነፍሱን ሰጠ።"11

ምህረታዊ ሞትም ከምድራዊ ህይወት ስቃይ ነጻ አድርጎት ወደ አባቱ ፊት መለሰው።

በመጨረሻው ጊዜም መምህሩ ለመመለስ ይችል ነበር። ነገር ግን አላደረገም። ሁሉንም ነገሮች ያድን ዘንድ፣ ከሁሉም በታች አልፎ ሄደ። ህይወት የሌለው ሰውነቱም በቶሎነትም ቢሆን በክብር በተበደረ መቃብር ውስጥ ተቀበረ።

በሳምንቱ መጀመሪያ ቀን የጌታን ሰውነት ለመንከባከብ መግደላዊት ማሪያም እና ሌላዋ ማርያም ወደመቃብሩ ሲሄዱ መላእክቱ የነገራቸው ቃል ለእኔ ታላቅ ትርጉም አለው። "ሕያውን ከሙታን መካከል ስለ ምን ትፈልጋላችሁ? ተነሥቶአል እንጂ በዚህ የለም።"

አዳኛችን እንደገና ኖሯል። ከህይወት ታሪክ ሁሉ ግርማዊ፣ አፅናኚ፣ እና አረጋጋጭ የሆነው ነገር፣ እንዲሁም ከሞት ላይ ድል ማግኘት ደርሷል።የገትሰመኔ እና የካልቨሪ ስቃይ ጠፋ። የሰው ዘር ደህንነትም ተረጋገጠ። የአዳም ውድቀትም እንደገና ተነስቷል።

ኢዮብ "ሰው ከሞተ ተመልሶ ሕያው ይሆናልን?" ብሎ ለጠየቀው መልስ የመጀመሪያእ ትንሳኤ ባዶ መቃብር መልስ ሰጥቷል።፡ ድምጼል ለሚሰሙት ሁሉ ሰው ከሞተ ተመለሶ ህያው ይሆናል በማለት አውጃለሁ። ይህን የምናውቀውም በተገለጸ እውነት ብርሀን ስላለን ነው። "ሞት በሰው በኩል ስለ መጣ ትንሣኤ ሙታን በሰው በኩል ሆኖአልና። ሁሉ በአዳም እንደሚሞቱ እንዲሁ ሁሉ በክርስቶስ ደግሞ ሕያዋን ይሆናሉና።"13

የክርስቶስን መሰቀል ሀዘንን እና ከሞት የመነሳቱን ደስታ አጋጣሚ የነበራቸውን ምስክሮች አንብቤአለሁ እናም አምናለሁ። ከሞት በተነሳው ጌታ የተጎበኙት የአዲሱ አለም ህዝቦች ምስክሮችንም አንብቤአለሁ እና አምናለሁም።

በዚህ ዘመን በቅዱስ ጥሻ ውስጥ ከአበ እና ወልድ ጋር የተነጋገረውን እና ምስክሩን በደሙ ያተመውን ምስክርም አምናለሁ። እንዲህም ገልጿል፣ "እናም አሁን፣ ስለእርሱ ከተሰጡት ብዙ ምስክሮች በኋላ፣ ይህም በመጨረሻ ስለእርሱ የምንሰጠው ምስክር ነው፤ ህያው ነው! በእግዚአብሔር ቀኝ እጅ በኩልም አይተነዋልና፤ እናም እርሱ የአብ አንድያ ልጅ እንደሆነም ሲመሰክር ድምፅ ሰምተናል።"14

የሞት ጭለማ በተገለጸ እውነት ብርሀን ሊበተን ይችላል። መምህርም እንዲህ አለ፣ "ትንሣኤና ሕይወት እኔ ነኝ።15 "ሰላምን እተውላችኋለሁ፥ ሰላሜን እሰጣችኋለሁ፤ እኔ የምሰጣችሁ ዓለም እንደሚሰጥ አይደለም።"16

ከሞት ስለመነሳት እውነትነት ከሚመሰክሩት እና በአዳኝ ቃል የተገባውን ሰላም እና መፅናኛን በሚያስፈልጋቸው ጊዜ ከተቀበሉት ምስክርን ባለፉት ብዙ አመቶች የተቀበልኩትን ለመቁጠር አልችልም።

የአንዱን ታሪክ ክፍል ከእናንተ ጋር ልካፈል። ከሁለት ሳምንት በፊት  በአስራ አንድ አመቱ ስለታመመበት ልጁ ጄሰን እና ስለቤተሰቡ ስሜታን የሚነካ ደብዳቤ ከአንድ አባት ደረሰኝ። ለብዙ አመቶች የጄሰን በሽታ እየደጋገመ መጣ። ይህም አባት ምንም እንኳን የጤንነት ፈተና ቢኖረውም ጄሰን እንዴት ጥሩ አመለካከት እንደነበረው ተናገረ። በ12 አመቱ ጄሰን የአሮናዊ የክህነት ስልጣንን ተቀበለ እና "ሀለፊነቱን ጤንነቱ ጥሩም ይሁን ወይም አይሁን በጥሩ ለማሟላት ሁልጉዜም ሞከረ።"12 የ<u> Eagle Scout ሽልማቱንም በ14 አመቱ ተቀበለ።</u>

ባለፈው በጋ በ15 አመቱ አካባቢ እንደገና ወደ ሆስፒታል ገባ። አንድ ጊዜ አባትየው ጄሰንን ሲገበኘው አይኑን ጨፍኖ አገኘው። እንደተኛ ወይም እንዳልተኛም ባያውቅም፣ በጸጥታ ያነጋግረ ጀመረ። እንዲህም አለው፣ "ጄሰን በአጭሩ ህይወትህ ብዙ ነገሮች እንዳለፈብህ እና የአሁኑ ጉዳይህ አስቸጋሪ እንደሆነ አውቃለሁ። ምንም እንኳን ወደፊት ታላቅ ፈተና ቢኖርብህም፣ በኢየሱስ ክርስቶስ ያለህ እምነትህን አትጣል።" በእርግጠኛ ድምፅም "አላጣም" ብሎ ጄሰን ሲመልስበት አስደነገጠው። ጄሰን ከዛም አይኑን ጨፈነ እና ምንም ተጨማሪ አላለም።  በዚህ መልሱ ከዚህ በፊት ከሰማሁት ምስክሮች

ሁሉ በላይ ሀይለኛ እና ንጹህ የሆነ ምስክርን ሰማሁ። መልሱ በእዛ ቀን በነፍሴ ላይ ታተመ፣ የሰማይ አባቴ የዚህ አስደናዊ እና ክብራዊ ወንድ ልጅ አባት እንድሆን ስለባረከኝም ልቤ በደስታ ተሞላ። …ይህም ስለክርስቶስ ስላለው ምስክር ሲገልፅ የሰማሁት ለመጨረሻ ጊዜ ነበር ።”

ምንም እንኳን ቤተሰቡ ይህ ሌላ የሆስፒታል ቁየታ እንደሆነ ቢመስላቸውም፣ ከሁለት ሳምንት በኋላ ጄሰን ሞተ። በዚያም ጊዜ ታላቅ ወንድሙና እህቱ በሚስዮን ያገለግሉ ነበር። ሌላው ወንድም ካይልም ወደ ሚስዮን ተጠርቶ ነበር። ጥሪው የመጣውም ጄሰን ከመሞቱ አንድ ሳምንት በፊት ነበር እና ቤተሰቦች በሙሉ በሆስፒታል ክፍል ተሰብስበው የካይልን የሚስዮን ጥሩ ለመክፈት ችለው ነበር።

በጻፈልኝ ደብዳቤ አባትየው ጄሰን በሆስፒታል መኝታው ላይ እያለ ካይል የሚስዮን ጥሩ ወረቀቱን ይዞ ተነስቶ የነበረበትን ፎቶ ላከልኝ። በፎቶው ላይም “በመጋረጃው ሁለትም በኩል ለሚስዮናቸው ለማገልገል የተጠሩት” የሚል ርዕስ ነበረ።

በሚስዮን ያገለግሉ የነበሩት የጄሰን ወንድምና እህት የሚያፅናና ደብዳቤ በጄሰን መቃብር ጊዜ እንዲካፈል ልከው ነበር። በአርገንቲና የምታገለግለው እህቱ እንዲህ ጻፈች፣ “ኢየሱስ ክርስቶስ ህያው እንደሆነ አውቃለሁ እና ህያው ስለሆነም ውድ ወንድማችን ጄሰን እና ሁላችንም እንደገና ህያው እንሆናለን።…እንደዘለአለም ቤተሰብ መተሳሰራችንን ስለምናውቅ መፅናኛ እናገኛለን። በዚህ ህይወት ታዛዥ ለመሆን እና ጥሩ ለማድረግ የምንችለውን ሁሉ ካደረግን፣ እርሱንም እንደገና እናየዋለን።” እንዲህም ቀጠለች፣ “በዚህ ጊዜ የምወደው ቅዱስ መጻህፍት ጥቅሰት አዲስ ትርጉም እና አስፈላጊነት አለው፣ በራዕይ ምዕራፍ 21 ቀጥር 4 ውስጥ ‘እንባዎችንም ሁሉ ከዓይኖቻቸው ያብሳል፥ ሞትም ከእንግዲህ ወዲህ አይሆንም፥ ኀዘንም ቢሆን ወይም ጩኸት ወይም ሥቃይ ከእንግዲህ ወዲህ አይሆንም፥ የቀደመው ሥርዓት አልፎአልና።’”

ውድ ወንድሞቼ እና እህቶቼ፣ በዝልቅ ሀዘናችን በዚያ ትንሳኤ ጠዋት “እንደ ተናገረ ተነሥቶአልና በዚህ የለም” ካለው ታላቅ ሰላም ልናገኝ እንችላለን።

ተነስቷል! ተነስቷል!<br>
በደስታ ድምፅ አውጁት።<br>
የሶስ ቀን እስር ቤቱን ሰብሯል፤<br>
አለም በሙሉ ይደሰት።<br>
ሞት ተሸንፏል፣ ሰው ነጻ ነው።<br>
ክርስቶስ ድል አድርጓል!17

በምድር እንደእርሱ ልዩ ምስክር አንዱ፣ በዚህ ግርማዊ የትንሳኤ ሰንበት ይህ እውነት እንደሆነ የማውጀው በቅዱስ ስሙ፣ እንዲሁም በአዳኛችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ነው፣ አሜን።